GAR

# በመንግስት ድጋፍ ካናዳ ስደተኞችን መልሶ የማቋቋም ፕሮግራም

## ስደተኞችን ካናዳ መልሶ ማቋቋም
## ጠቃሚ መረጃ

እርስዎ ካናዳ መጥተው ኑሮዎን መመስረት ይፈልጋሉ:: የካናዳ መንግስት ባለስልጣናትም ማመልከቻዎትን ተቀብለው ማድረግ ያለባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ አጠናቀዋል:: አሁን ከዚህ የሚቀጥለው ሂደት ምን እንደሆነ ለማወቅ ያሰቡ ይሆናል:: የእርስዎን የስደተኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ለካናዳ ነዋሪነት ማመልከት እንደሚችሉ ውሳኔ ላይ መደረሱ በራሱ በመልሶ መቋቋም ሂደቱ ላይ በጣም ወሣኝ እርምጃ ሲሆን የመጨረሻው የውሳኔ ደረጃ ግን አይደለም::

**ይህ ሰነድ ማመልከቻዎትን በተመለከተ ቀጣዮቹ ሂደቶች ምን እንደሚሆኑ የሚያሳይና ስለካናዳም አንዳንድ ግንዛቤ የሚሰጥ መረጃን ያካትታል::**



Immigration, Refugees and Citizenship Canada
Immigration, Réfugiés et Citoyenneté Canada

Canada

© በፍልሰትና ዜግነት ሚኒስቴር ተወካይነት የሚከበር የግርማዊት ንግስት መብት በካናዳ 2019

Ci44-20/2019Amh-PDF
978-0-660-32874-4
2627-11-2019

## በመንግስት የሚደገፍ የስደተኞች ፕሮግራም

በመንግስት በሚደገፈው የስደተኞች ፕሮግራም አማካኝነት ካናዳ የመኖር ዕድል ሊኖርዎት ይችል ይሆናል:: ይሄም የሚያመላክተው ካናዳ እርስዎን በስደተኝነት ተቀብላ ነዋሪ እንድታደርግዎ በተባበሩት መንግሥታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽን ወይንም በሌላ ስደተኞችን የሚደለድል ወይንም የሚጠቁም ድርጅት አማካኝነት መጠየቋን ነው::

ማመልከቻዎ ተቀባይነት ካገኘ ለመጀመሪያው ዓመት የካናዳ ኑሮዎ የሚያስፈግዎትን የገንዘብ ድጋፍ ከካናዳ ፌደራል መንግስት ወይንም የኪውቤክ ክፍለሀገር መንግስት ያገኛሉ:: ወጭያቸው በካናዳ መንግስት የሚሸፈኑና ለአዲስ ካናዳ መጪዎች የሚሰጡ የተለያዩ ድጋፎችን አገልግሎት ሰጪ በመባል በሚታወቁ ድርጅቶች አማካኝነት ያገኛሉ:: የእነኚህ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ፍላጎትም የካናዳ ሕይወትዎን በተሳካ ሁኔታ መቀጠል እንዲችሉ ድጋፍ ማድረግ ነው::

## የማመልከቻው ሂደት ስርዓት - ቀጣይ አርምጃዎች

- እርስዎና ቤተሰብዎ ወደ ካናዳ ከመምጣታችሁ በፊት የጤና ምርምራ ማድረግ ይኖርባችኋል።
- የምረመራውንና ሌሎችም ካናዳ ከመሄድዎ በፊት የሚያስፈልግዎትን አንዳንድ የህክምና አገልግሎቶች ወጪ የካናዳ መንግስት ይሸፍናል::
- እርስዎና ቤተሰብዎ ወደ ካናዳ ከመምጣታችሁ በፊት የጤና ምርምራ ማድረግ ይኖርባችኋል።
- የምረመራውንና ሌሎችም ካናዳ ከመሄድዎ በፊት የሚያስፈልግዎትን አንዳንድ የህክምና አገልግሎቶች ወጪ የካናዳ መንግስት ይሸፍናል::
- ቃለ መጠይቅ ከተደረገልዎት በኋላ የጤና ምርመራ እንዲያደርጉ ሳይጠየቁ ብዙ ወራት ሊወስድ ይችላል:: የጤና ምርመራዎን ያላጠናቀቁ ከሆነ ተጨማሪ መረጃ በመያዝ የአለም ዓቀፉ የሰዎች ፍልሰት ድርጅት (አይኦኤም/IOM) ወይንም የካናዳ የኢሚግሬሽን ስደተኞችና ዜግነት መስሪያቤት ከእርስዎ ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ::
- ከወንጀል ነፃ መሆንዎትንና ለካናዳ የሰላም ስጋት እንደማይሆኑ ለማረጋገጥ ሲባል ምርመራ የማድረግ ግዴታ ይኖርብዎታል:: ይህን ማድረግዎ ምንም ከባድ ወንጀል ፈፅመው እንደማያውቁና ወደፊትም ለካናዳ ደህንነት ስጋት እንደማይሆኑ ያረጋግጣል::
- የካናዳ ባለስልጣናት ማመልከቻዎትን በመመርመር የሕክምና፣ የደህንነትና፣ የወንጀል ምርመራዎችን ማለፍዎትን ያረጋግጣሉ። እርስዎ ግን እስካልተጠየቁ ድረስ ምንም ተጨማሪ መርጃ መስጠት አይኖርብዎትም::
- የሕክምና፣ የደህንነትና፣ የወንጀል ምርመራዎችን ማለፍ ሳይችሉ ከቀሩ ካናዳ በነዋሪነት ለመምጣት ላይመረጡ ይችላሉ::
- የሕክምና፣ የደህንነትና፣ የወንጀል ምርመራዎችን ካለፉ ደግሞ እርስዎና ቤተሰብዎ ወደ ካናዳ ለመምጣት ለምታደርጉት ዝግጅት እገዛ እንዲያደርጉላችሁ ካናዳ የአለም ዓቀፍ የሰዎች ፍልሰት ድርጅትን (አይኦኤም) ወይንም ሌላ ድርጅትን ትጠይቃለች።
- ወደ ካናዳ ከመሄድዎት በፊት በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚረዳ መረጃ የሚሰጥበት ዝግጅት ላይ በነፃ እንዲሳተፉ የሚጋብዙ አንዳንድ ሀገሮች አሉ:: ይህም የነፃ ዝገጅት “በውጪ አገር ካናዳን ማስተዋወቂያ ዝግጅት” በመባል ይታወቃል። የዚህን ዝግጅት ወጪ የሚሸፍነው የካናዳ መንግስት ሲሆን ዝግጅቱን የሚያስተባብረውና የሚያቀርበው ደግሞ የአለም ዓቀፍ የሰዎች ፍልሰት ድርጅት (አይኦኤም) ይሆናል። እርስዎ ባሉበት ሀገር ይሄ ዕድል ካለ በዝግጅቱ ቢሳተፉ ስለካናዳ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖርዎት ከማድረግ ባሻገርም ካናዳ ከደርሱ በኋላ ተመቻችተው መኖር ይችሉ ዘንድ የሚያግዙዎትንና ሊያገኙ ስለሚችሏቸው አግልግሎቶች ጠቃሚ መርጃ ያገኙበታል።

## ጉዞ ወደ ካናዳ




- ሁሉንም ምርመራዎች ካለፉና ሰነዶችዎ ከተዘጋጁ በኋላ ወደ ካናዳ ለሚያደርጉት ጉዞ አስፈላጊው ዝግጅት ይከናወናል።
- አንዳንድ ሀገሮች ለሀገር መውጭያ ቪዛ ክፍያ ያስከፍላሉ። እርስዎ ያሉበት ሀገርም ይህን ክፍያ የሚጠይቁ ከሆነ ክፍያውን መክፈል የእርስዎ ግዴታ ነው። ነገርግን የአለም ዓቀፍ የሰዎች ፍልሰት ድርጅት (አይኦኤም) ጉዳዩን በማስፈፀም በኩል ሊያግዝዎት ይችላል።
- ፓስፖርት ወይንም ሌላ ሕጋዊ የመጓጓዣ ሰነድ የሌለዎት ከሆነ ወደ ካናዳ መሄድ የሚያስችልዎትን ሰነድ የካናዳ መንግስት ይሰጥዎታል።
- ወደ ካናዳ የሚጓዙበትን ወጪ መሸፈን የሚችል ገንዘብ የካናዳ መንግስት በብድር መልክ ይመድባል።
- ይህም ገንዘብ ብድር ስለሆነ ሙሉውን ዕዳ ለካናዳ መንግስት እንደ እዳው ክብደት ከሶስት አስከ ስምንት ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ ጨርሰው መክፈል ይኖርብዎታል።
- የእዳውን ክፍያ ካናዳ በገቡ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መጀመር ይኖርብዎታል።
- ወደ ካናዳ ጉዞዎን ሲያደርጉ አውሮፕላን ማረፊያ መድረስ እንዲችሉ ከዛም በኋላ ከኢምግሬሽን ባለስልጣናት ጋር ለሚኖርዎት ጥያቄና መልስ እገዛ ያገኛሉ።
- የመጨረሻ መዳረሺያዎ የሆነው የካናዳ ከተማ መድረስ በጣም ረጅም ጊዜ የሚወስድ ሊሆን ይችላለ። አውሮፕላን ማረፊያና አውሮፕላን ውስጥ ለምግብ መክፈል ሊኖርብዎት ስለሚችል ሊበሉት የሚችሉትን ትንሽ ምግብ መያዝ አይዘንጉ።

- መጀመሪያ ካናዳ ደርሰው ከአውሮፕላን ሲወርዱ የአገልግሎት ሰጪ መስሪያቤት ሰራተኛ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአስተርጓሚ ጋር በመሆን ይቀብሉዎትና ወደ ካናዳ ለመግባት የሚያስፈልግዎትን የኢሚግሬሽን ጥያቄ በመመለስና ቅፅ በመሙላት ያግዙዎታል።
- መኖሪያዎ ወደሆነው ከተማ ለመዝለቅ ሌላ የአውሮፕላን በረራ ማድረግ ካለብዎት ደግሞ እነኚህ ሰዎች ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ያግዙዎታል። ቀጣዩን አውሮፕላን ለመያዝ ረጅም ጊዜ የሚያስጠብቅዎት ከሆነ ደግሞ ምግብና የበረራው ሰዓት እስኪደርስ የሚተኙበት ስፍራ ያዘጋጁልዎታል።
- የመጨረሻ መዳረሻ ከተማዎ ደርሰውም ከሆነ በአካባቢው ያለ አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች አውሮፕላን ማረፊያው ድረስ በመምጣት እርስዎን ለመቀበል ስለሚጠብቁ መጀመሪያ የተቀበሉዎት ሰዎች ከእነርሱ ጋር ያገናኙዎታል።
- የሚቀበሉዎት የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሰራተኞችም የሚያርፉበት የእንግዳ መቀበያ ቤት ወይም ሆቴል ወይንም የመኖሪያ አፓርትመንት ይሰጡዎታል።
- አንዳንድ ጊዜ በዘላቂነት የሚኖሩበት ስፍራ ተገኝቶ እስኪገቡ ድረስ ለጥቂት ቀናት ወይንም ሳምንታታ በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ስፍራ ሊሰጥዎት ይችላል።
- የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች በመንግስት የሚደረግልዎትን የገንዘብ ድጋፍ በመጠቀም ልብስና ምግብ መግዛት እንዲችሉ እገዛም ያደርጉልዎታል። በተጨማሪም የክረምት አልባሳትም ሊሰጥዎ ይችል ይሆናል።
- የአካባቢው አገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሰራተኞች የሚከተለውን ለማድረግ እገዛ ያደርጉልዎታል፡
  - የሚኖሩበት ክፍለሀገር የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ማመልከቻ ማስገባት፣
  - የቤተሰብ ህክምና ዶክተርና የጥርስ ሀኪም ማግኘት፣
  - የትምህርት ስርዓቱን የሚገልፅ መረጃ ማግኘትና ልጆችዎትን ትምህርትቤት ለማስመዝገብ ድጋፍ ማድረግ፣
  - ቅፆችንና ማመልከቻዎችን መሙላት፣
  - የንግግር አስተርጓሚና የጽሁፍ ተርጓሚ ማግኘት፣
  - ከእርሶ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች መፈለግና ማገናኘት፣
  - የባንክና የህዝብ መጓጓዣ አጠቃቀም፣
  - እርስዎና ቤተሰብዎ የሚያስፈልጓችሁን ነገሮች መገምገምና በሚኖሩበት አካባቢ ለሕዝብ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ማገናኘትና፣
  - የቋንቋ ብቃቶትን ማጎልበትና ለስራ ዝግጁ እንዲሆኑ ማገዝን የመሳሰሉ አግልግሎቶች።

አዲስ ሕይወት በካናዳ መመስራት ይችሉ ዘንድ መንግስት የመቋቋሚያ ድጋፍ ያደርግልዎታል። ይሁን እንጂ ስለዚህ ስለሚያገኙት ድጋፍ መጠን የተጋነነ ግምት እንዳይኖርዎት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

የካናዳ ኑሮዎት የተሳካ እንዲሆንልዎት በትጋት ለመስራት መዘጋጀት ይኖርብዎታል።

ከመንግስት የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ የሚቆየው ካናዳ ከገቡበት ቀን ጀምሮ አንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ሲሆን ዓመቱ ከመሙላቱ በፊት እራስዎትንና ቤተሰብዎትን ለመደገፍ የሚችሉበት ሁኔታ ካገኙ ከመንግስት የሚያገኙት የገንዘብ ድጋፋ ይቋረጣል። ካናዳ መጥተው አንድ ዓመት ከሞላዎት በኋላ ግን እራስዎትንና ቤተሰብዎትን መደገፍ የእርስዎ ሀላፊነት ነው።

# ከቤተሰብዎ ጋር የካናዳ ሕይወትዎን መጀመር



እርስዎና የትዳር ጓደኛዎ፣ በእርስዎ ስር የሚተዳደሩ ልጆች፣ በእርስዎ ስር የሚተዳደሩ ማንኛቸውም ልጆች ደግሞ ልጅ ካላቸው እነሱንም ጨምሮ በአንድ የኢሚግሬሽን ቅጽ ላይ በማመልከት አንድ ላይ ካናዳ መምጣት ትችላላችሁ።

ወደ ካናዳ ከመጓዝዎ በፊት በጋብቻ ሁኔታዎ ላይ ምንም አይነት ለውጥ ካለ (ለምሳሌ ቢያገቡ ወይም ቢፈቱ) ወይም ልጅ ቢወልዱ ለተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽንና (ዩኤንኤቸሲአር/UNHCR) ለካናዳ የስደተኞች ጉዳይ ባለስልጣን ማሳወቅ አለብዎት። ይህን የሚያደርጉትም አዲሶቹ የቤተሰብዎ አባላት በእርስዎ የኢሚግሬሽን ማመልከቻ እንዲካተቱ ለማስቻል ነው።



ካናዳ መኖር የሚፈልጉት ከሙሉ ቤተሰብዎ ጋር መሆኑን ለካናዳ ባለስልጣናት ማሳወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ወደ ካናዳ ከመሄድዎ በፊት ስለባለቤትዎና ልጆችዎ ለካናዳ ባለስልጣናት ያላሳወቁ ከሆነ ካናዳ ከገቡ በኋላ ወደ እርስዎ ዘንድ ማምጣት (ስፖንሰር ማድረግ) ቢፈልጉ አይችሉም።

ዘመዶች ወይም የቅርብ ጓደኞች ካናዳ ያሉዎት ከሆነና ከእነርሱ ጋር በቅርበት መኖር የሚፈልጉ ከሆነ ይህንኑ ለዩኤንኤቸሲኣርና/UNHCR ለካናዳ ባለስልጣናት ያሳውቁ። ካናዳ በተቻለ መጠን ስደተኞቹ የሚያውቋቸው ሰዎችን ድጋፍ በሚያገኙበት ማኅበረሰብ አካባቢ ለማኖር ጥረት ታደርጋለች።

ምናልባት "አብሮዎት የሌለ" ጥገኛ የቤተሰብ አባል እንዳለዎት በማመልከቻዎት ጠቅሰው ሊሆን ይችላል። ይህን አድርገው ከሆነ አንዴ ካናዳ ከገቡ በኋላ ይህን የቤተሰብ አባል "የአንድ ዓመት የእድል መስኮት" በመባል በሚታወቅ ፕሮግራም አማካኝነት ወደ ካናዳ ማምጣት ይችላሉ። ካናዳ በገቡ አንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የትዳር ጓደኛዎ፣ ጥገኛ ልጆች፣ የእርስዎ ጥገኛ የሆኑ ልጆችዎት ልጆች፣ ወደ ካናዳ እንዲመጡልዎት ማመልከት ይችላሉ። ይህን ማድረግ የሚችሉት ግን ወደ ካናዳ ከመጓዝዎ በፊት እነኚህ ጥገኞችዎት በሙሉ በማመልከቻዎት ላይ የተመዘገቡ ከሆኑ ብቻ ነው።

ሌሎች የቤተሰብ አባሎች ለምሳሌ ወላጆች፣ አያቶች፣ ወንድሞችና እህቶች፣ በግላቸው ለካናዳ ነዋሪነት ማመልከቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል። አርስዎ አንዴ ካናዳ ነዋሪ ከሆኑ በኋላ የተወሰነ ቅድመ ሁኔታዎችን ካሟሉ የቤተስብ አባልዎ የሆኑ ሰዎችን ለማስመጣት ማመልከት ይችላሉ። በሁለቱም መንገድ ቢሆን እነኚህን የቤተሰብ አባላት ወደ ካናዳ ማምጣት በጣም ረጅም ጊዜ ስለሚፈጅ የቤተሰብ አባልዎን በጣም ለረጅም ጊዜ ሳያዩ ሊቆዩ ይችላሉ።

የካናዳ ኢሚግሬሽን ስደተኞችና ዜግነት ቢሮ ማመልከቻው በጣም በበቂ ምክንያት ታግዞ ተቀባይነት ካላገኘ በስተቀር የቤት ለማዳ እንስሳትን ወደ ካናዳ ለማጓጓዝ ሁኔታዎችን አያመቻችም። ስለዚህም ስደተኞች ለማዳ እንስሶቻቸውን ወደ ካናዳ ይዘው መምጣት የሚያስቡ ከሆነ አስፈላጊውን የመጓጓዣ ሁኔታ እራሳቸው ማመቻቸት አለባቸው።

## የካናዳ ነዋሪነትዎ ሁኔታ

ካናዳ እንደደረሱ የቋሚ ነዋሪነት ማረጋገጫ የሚል ሰነድ ይሰጥዎታል። ይህም ሰነድ እዚህ ሀገር በቋሚ ነዋሪነት መኖር ይችላሉ ይላል። ይህም የሚያረጋግጠው በቀጣይ የሕይወት ዘመንዎ በሙላ ካናዳ በሕጋዊነት ሊቆዩ መቻልዎትን ነው። ስራ ለመስራትም ይሁን ትምሕርት ቤት ለመግባት ይችላሉ።

የካናዳ ዜጋ ለመሆን ማመልከት እንዲችሉ ካናዳ ለምን ያክል ጊዜ መኖርና ካናዳ ውስጥ በአካል መቆየት እንዳለብዎት የሚያሳዩ ልዩ መስፈርቶች አሉ። አስፈላጊ መስፈርቶቹን በሙሉ ካሟሉ በኋላ የካናዳ ዜጋ ለመሆን ማመልከት ይችላሉ።

ለበለጠ መረጃ ይህንን ይጫኑ https://www.canada.ca/en/immigration-refugees-citizenship/services/canadian-citizenship/become-canadian-citizen.html.

## ካናዳ የት እንደሚኖሩ





ካናዳ በስፋት ከዓለም ሁለተኛዋ ሀገር ስትሆን ብዙ ትልልቅ ከተማዎችና መንደሮች እንዲሁም በጣም ጥቂት ወይንም ፈጽሞ ሰው ያልሰፈረባቸው በርካታ አካባቢዎችም አሏት። አብዛኛዎቹ ዋና ዋና ከተሞች የሚገኙት በካናዳ ደቡባዊ ክፍል አሜሪካን ድንበር አቅራቢያ ነው።

ብዙዎቹ ህዝቦች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች በጣም የተራራቁ በመሆናቸው በአውሮፕላንም ሳይቀር ከአንዱ ከተማ ወደሌላ ለመሄድ ረጅም ሰዓታት ያስፈልግዎታል። ለምሳሌ በቶሮንቶና በቫንኩቨር ከተማዎች መካከል ያለው ርቀት ከ4,300 ኪሎሜትር በላይ ሲሆን በአውቶቡስ ጉዞ ወደ ሶስት ቀናት ያክል ይወስዳል።

እርስዎም ከበርካታ ከተማዎች ውስጥ በአንዱ እንዲኖሩ ሊመደቡ ይችላሉ። ካናዳ ነዋሪ የሆኑ ቤተሰቦች ወይንም የሚያውቋቸው ሰዎች ካሉ በተቻለ አቅም ለእነርሱ ቀረብ ያለ ከተማ እንዲኖሩ ለማድረግ ጥረት እናደርጋለን። ነገር ግን የሚኖሩበትን ከተማ ለመወሰን ኢንዲቻል ከግምት የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ አስፈላጊ የሆኑ የተለዩ አገልግሎቶች መኖር፣ የመኖሪያ ቤት መገኘት፣ የማህበራዊ አገልግሎቶች መኖርና፣ የቤተሰብዎ አባላት ቁጥር ለሚመደቡበት ከተማ ምርጫ ወሳኝ ጉዳዮች ሊሆኑ ይችላሉ።
ካናዳ ነዋሪ የሆኑ ቤተሰቦች ወይንም የሚያውቋቸው ሰዎች የመኖሪያ ከተማቸውን ከቀየሩ መስርያቤቱን በአስቸኳይ ያሳውቁ። 5

መኖሪያዎን ካናዳ ውስጥ ወደሌላ ቦታ የመቀየር መብትዎ የተከበረ ቢሆንም መጀመሪያ በተመደቡበት ቦታ ቢያንስ ለአንድ ዓመት ያክል እንዲቆዩ እናበረታታዎታለን። ይህን ቢያደርጉ ደግሞ ለእርስዎ ተብለው የተዘጋጁትን አገልግሎቶች በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ያስችልዎታል።

## የካናዳ ማኅበረሰብ



ወንዶችና ሴቶች ካናዳ ውስጥ እኩል ናቸው:: ሁለቱም ፆታዎች ያላቸውም መብት ተመሳሳይ ሲሆን እኩል አክብሮትም አላቸው:: የሁሉም አይነት ማኅበራዊ ክፍሎች፣ ባሕሎች፣ ዘሮችና ሃይማኖቶች ወንድና ሴት ብለው ሳይለያዩ ያለገደብ አብረው ይቀላቀላሉ በእኩልነትም ይስተናገዳሉ::

ያለዎትን አስተያት ካናዳ ውስጥ በነጻነት መናገር የሚችሉ ሲሆን እርስዎም ሌሎች ሰዎች ተመሳሳይ መብት እንዳላቸው በመገንዘብ መብታቸውን ሊያከብሩ ይገባል::

እርስዎ ሊሳተፉባቸው የሚችሉ በርካታ የወንዶች የሴቶችና የልጆች ማህበራዊ ስብስቦችና ማህበሮች አሉ:: እንደቤተሰብ በጋራ ሊሳተፉባቸው የሚችሉ እግርኳስና ዋና የመሳሰሉ የስፖርትና ሌሎችም ዝግጅቶች አሉ:: እነኚህም ዝግጅቶች አንዳንዶቹ ነፃ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ያስከፍላሉ::

ከአሁን በፊት በመላው ቤተሰብዎ ተከበው በእነሱ መረዳትና መደገፍ ለምደው ሊሆን ይችላል:: ካናዳ ከገቡ በኋላ ግን ብቸኝነት ሊሰማዎት ይችላል:: ነገር ግን አሁንም ብቻዎትን እንዳልሆኑ ይወቁ:: የሚያሳስብዎ ጉዳይ ካለ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅት ሰራተኛን ወይንም አንዱን የማኅበረሰብዎን አባል ያነጋግሩ:: ካናዳ የጀመሩት ሕይወት የተሳካ እንዲሆን መርዳት የሚችሉና የሚፈልጉ ሰዎች አሉ::

በሚኖሩበት አካባቢ አዲስ ለመጡ ሰዎች የተዘጋጁ ስብሰባዎች ካሉ ለመሳተፍ ይሞክሩ:: ይህን ማድረግም በሚኖሩበት አካባቢ ጓደኛ ለማፍራትና በአካባቢዎ ስላሉ አገልግሎቶች ግንዛቤ እንዲኖርዎት በማድረግ ይረዳዎታል::

## የካናዳ ሕግጋት/ሕጎች




የካናዳ ሕግጋት የሁሉንም ሰዎች መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች እኩለንትንና ነፃነትን ጨምሮ እውቅና ይሰጣሉ ያስከብራሉም:: የካናዳ መብቶችና ነፃነት ቻርተር የካናዳ ህገመንግስት አካል ሲሆን የካናዳን ምድር ከረገጡበት ጊዜ ጀምሮ መብትዎንና ነፃነትዎን ይከላከልልዎታል::

እርስዎ የመጡበት ሀገር ህገወጥ ተደርጎ የማይታይ አንዳንድ ድርጊት ካናዳ ውስጥ ሕግን የሚፃረር ሊሆን እንደሚችል ያስተውሉ:: ሴትንና ልጅን መምታት፣ ሕፃን ልጅን ያለአዋቂ ጥበቃ ለብቻ ትቶ መሄድ፣ ያለኢንሹራንስ ወይንም መንጃ ፍቃድ መኪና መንዳትና፣ ልጆች የወንበር ማሰሪያ ቀበቶ ሳይደርግላቸው መኪና መንዳት እንደ ህገወጥነትና እንደወንጀል ይታያሉ:: በርካታ የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች በየቦታው ያሉ ሲሆን ሕዝብ ባለበትና ለመፀዳጃነት ከተዘጋጁ ስፍራዎች ውጭ ሽንት መሽናትና መፀዳዳት ህገወጥነት ነው::

የካንዳን ሕግጋትና የፍትህን ስርዓት በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከፈልጉ የካናዳ መንግስት የኢንተርኔት ገፅ ላይ ማግኘት ይችላሉ::

## ቋንቋ




ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ሁለቱ የካናዳ የመንግስት የስራ ቋንቋዎች ናቸው። ስለዚህም የፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ እውቀት ካናዳ ውስጥ ተመቻችተው ለመኖር በጣም ይጠቅምዎታል።
በአብዛኛው ክፍለሀገራትና ግዛቶች (ቴሪተሪዎች) በሰፊው የሚነገረው እንግሊዝኛ ነው። ኪውቤክ ክፍለሀገር ደግሞ በዋናነት የሚነገረው ፈረንሳይኛ ሲሆን በሁሉም የተቀሩት ክፍለሀገራትና ግዛቶች (ቴሪተሪዎች) ውስጥ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ህዝቦች ይገኛሉ። ብዛት የሌላቸው እንግሊዝኛ ተናጋሪዎችም ኪውቤክ ውስጥ ይኖራሉ።


ጠንካራ የፈረንሳይኛ ወይንም የእንግሊዝኛ ብቃት መኖር ሥራ ለማግኘት፣ ትምህርት ቤት ለመሄድ፣ አግልግሎቶችን ያለችግር ለመጠቀምና፣ ጓደኞች ለማፍራት ይረዳል። ስለዚህ የሚችሉ ከሆነ ወደ ካናዳ ከመምጣትዎ በፊት የፈረንሳይኛ ወይንም እንግሊዝኛ ብቃትዎን ለማሻሻል ጥረት ያድርጉ።

ካናዳ ከመጡ በኋላ ክፍያው በመንግስት የሚሸፈን የነፃ ቋንቋ ትምህርት መከታተል ይችላሉ። አገልግሎት የሚሰጡት ድርጅቶች የቋንቋ ችሎታዎትን ለመመዘን የሚያስፈልገውን ፈተና እንዲወስዱና ለቋንቋ ትምህርት እንዲመዘገቡ አስፈላጊውን እገዛም ያደርጉልዎታል።

## ስራ ማግኘት







ምንም እንኳን በመጀመሪያው አመት የካናዳ ኑሮዎ እርስዎና ቤተሰብዎ የገንዘብ እርዳታ የምታገኙ ቢሆንም በተቻለ ፍጥነት ሥራ ይዘው እራስዎትንና እና ቤተሰብዎን ማስተዳደር መጀምር እንዲችሉ ዝግጅት ማድረግ መልካም ሀሳብ ነው።

የተሻለ እንግሊዝኛ ወይንም ፈረንሳይኛ መናገር ሲችሉ ደግሞ ስራ የማግኘት ዕድልዎ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ አብዛኛዎቹ ቁጥጥር የሚደረግባቸውና የሙያ ስራዎች የሚከተሉት መመዘኛዎች እንዲሟሉ ይጠብቃሉ:

- እንግሊዝኛ ወይንም ፈረንሳይኛ በደንብ መቻል፣
- ከሥራ ጋር የተዛመዱ ቋንቋዎችን በሙሉ ጠንቅቀው ማወቅ፣
- አንዳንድ ካናዳ ብቻ የምንጠቀምባቸው ሊሆኑ የሚችሉትን አባባሎችና ዘዬዎች ጭምር መረዳት መቻል፣

የሚችሉ ከሆነ በሙያዎት ሥራ ለማግኘት ምን የቋንቋ ብቃት እንደሚጠበቅብዎት ለማጣራት ይሞክሩ። አንድ ጊዜ ካና ከገቡ በኋላ ሥራ እንዲያገኙና የቋንቋ ማሻሻይ ትምህርትቤት እንዲገቡ የሚያግዝዎት ድጋፍ ከአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ያገኛሉ። በተጨማሪም እነኚህ ድርጅቶች ጠቃሚ መረጃ መለዋወጥ የሚያስችሉ ስብሰባዎች ስለሚያዘጋጁ በስብሰባዎቹ በመሳተፍ ተጠቃሚ ይሁኑ።

የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ፣ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም የሙያ ምስክር ወረቀት ያለዎት ከሆነ ካናዳ ውስጥ ተቀባይነት ላይኖራቸው ይችላል። ዲግሪዎ/የምስክር ወረቀትዎ ወይም ሌሎች የትምህርት መረጃዎችዎ ተቀባይነት ይኑራቸው ወይንም አይኑራቸው የሚወስነው እርስዎ የሚኖሩበት ክፍለ ሀገር መንግስት ወይንም ብቃትን የመገምገም ስልጣን ያለው ድርጅት ነው። አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶቹ ያለዎትን የትምህርትና ሙያ ብቃት ማስረጃ ለማስገምገም ምን ማድረግ እንዳለብዎት በማሳየት ድጋፍ ያደርጉልዎታል።

የካናዳ የስራ ልምድ ለማግኘት አንዱ ጥሩ ዘዴ የነፃ አገልግሎት መስጠት ነው። ምንም እንኳን ለነፃ አግልግሎቱ የገንዘ ክፍያ ባያገኙም ሥራ ማግኘት እንዲችሉ የሚያግዝዎት ጥሩ የስራ ልምድ፣ የስራ ክህሎትና የቋንቋ ብቃት ማዳበር ስለሚያስችልዎት በጣም ጠቃሚ መሆኑን አይዘንጉ። አዳዲስ ጓደኞች ለማፍራትና የሚኖሩበት ከተማ ውስጥ ካለው ሕብረተሰብ ጋር እንዲተዋወቁም ያግዝዎታል።

## የማቋቋሚያ አገልግሎቶች

የማቋቋሚያ አገልግሎቶች ወጪያቸው የሚሸፈነው በካናዳ የእሚግሬሽን ስደተኞችና ዜግነት መስሪያቤትና የኪውቤክ የኢሚግሬሽን የተለያዩ የህብረተሰብ አቀፍ ሚኒስቴር ነው፡፡ እነኚህ አገልግሎቶች ስደተኞችንም ጨምሮ ለሁሉም የካናዳ ቋሚ ነዋሪዎች በነፃ የሚሰጡ ሲሆኑ ካናዳ ኑሮ ለመመስረት ለሚያደርጉት ጥረት ይረዳዎታል፡፡

ካናዳ ከመምጣትዎ በፊት ለካናዳ ሕይወት በቂ ዝግጅት እንዲኖርዎት የሚያግዙ በርካታ ቅድመ ጉዞ አገልግሎቶች የካናዳ የእሚግሬሽን ስደተኞችና ዜግነት መስሪያቤት ቢሮ የኢንተርኔት ገፅ ላይ ማግኘትይችላሉ ፡፡ ማመልከቻዎት ተቀባይነት ማግኘቱን የሚያረጋግጥ ሰነድ ካገኙበት ጊዜ ጀምሮ ይህንን የኢንተርኔት መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

አንድ ጊዜ ካናዳ ከገቡ በኋላ የማቋቋሚያ አገልግሎት የሚሰጡት ድርጅቶች ሕይወትዎትን በካናዳ ለመመስረት የሚያግዙዎት የተለያዩ ድጋፎች ያደርጉልዎታል፡፡ እነኚህም አግለግሎቶች ሥራ ፍለጋ፣ የቋንቋ ትምህርት፣ ከሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ስልጠና ወይንም ትምህርት፣ ለአዛውንቶችና ወጣቶች ልዩ አገልግሎቶችን ያካትታሉ፡፡

በካናዳ የእሚግሬሽን ስደተኞችና ዜግነት መስሪያቤት ወጪያቸው የሚሸፈን አገልግሎቶች ሙሉ ዝርዝር ኢንተርኔት ላይ ይገኛል፡፡

## ወጪዎች

ካናዳ ከገቡበት ቀን ጀምሮ ለአስራ ሁለት ወራት ወይንም ከዚህ ጊዜ ቀድመው እራስዎትን እስኪችሉ ድረስ የካናዳ ፌዴራልመንግስት ወይንም የኪውቤክ ክፍለሀገር መንግስት የገንዘብ ድጋፍ ያደርግልዎታል፡፡

ይሄ የአስራ ሁለት ወራት የድጋፍ ጊዜ ካበቃ በኋላ ግን ምግብ፣ ቤት ኪራይ፣ መብራት፣ ውሀ፣ ልብስና፣ ታክስን ጨምሮ ወጪዎትን በሙሉ መሸፈን የእርስዎ ሀላፊነት ይሆናል፡፡ ገንዘቦትን እንዴት በጥንቃቄና በእቅድ መጠቀም እንደሚችሉ ማወቅ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

ከአስራ ሁለት ወራት በኋላ ሥራ ማግኘት ካልቻሉና ለቤተሰብዎ ድጋፍ የሚፈልጉ ከሆነ የተለያዩ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸወ የህብረተሰቡ አባላት ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶች ስላሉ እነሱን ማግኘት ይኖርብዎት ይሆናል፡፡ እነዚህ ድርጅቶችም የምግብ ባንክ ሌሎችም በጎ አድራጊ ድርጅቶችን ይጨምራሉ፡፡ በተጨማሪም ችግር ላለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦች የሚሰጡ የተለያዩ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ፕሮግራሞች አሉ፡፡ የዚህ ድጋፍ ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን ግን ማሟላት የሚኖርብዎት መመዘኛዎች አሉ፡፡

አገር ቤት ለሚገኙት ቤተሰብዎችዎ ገንዘብ መላክ ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህንን ማድረግ መብትዎ ነው።ይሁንና አብዛኛዉን ጌዜ ስደተኞች ራሳቸውን አስተዳድረው ከዚያ በኋላ ገንዘብ ተርፏቸው ወደቤተሰብ መላክ በጣም ይከብዳቸዋል፡፡ ካናዳ ብዙ ነገሮች እርስዎ ከሚጠብቁት በላይ ዋጋቸው ውድ ሁኖ ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ካናዳ ከሚያጋጥምዎ አዲስ ሕይወት ጋር መለማመድ ጊዜ እንደሚወስድም አይዝንጉ፡፡

## ትምሕርት ቤት



ልጆችዎ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርታቸውን በነፃ መከታተል ይችላሉ። እድሜያቸው ከስድስት እስከ አስራ ስድስት የሆኑ ሕጻናት በሙሉ ትምሕርት ቤት መሄድ አለባቸው። ይህን ማድረግም ሕጋው ግዴታ ነው። ብዙዎቹ ተማሪዎች እድሜያቸው ወደ 18 አካባቢ ሁኖ የምርቃት ዲፕሎማ እስኪያገኙ ድረስ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርታቸውን ይከታተላሉ።

ልጆቹ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርታቸውን ከጨረሱ በኋላ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ ሊገቡ ይችላሉ። ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲዎች ገንዘብ የሚያስከፍሉ ቢሆንም ተማሪዎቹ የነፃ ትምህርት ዕድል፣ የገንዘብ ድጎማና ብድር ማግኘት እንዲችሉ የሚያግዝ አቅምም ኮሌጅና ዩኒቨርሲቲዎች ይኖራቸዋል።

## የጤናና የጥርስ እንክብካቤ

እንደ ማንኛውም የካናዳ ቋሚ ነዋሪ ሆስፒታል መሄድና ዶክተር ማየትን ጨምሮ ለአብዛኛው የህክምና አገልግሎት ምንም ክፍያ መክፈል አይኖርብዎትም።



ካናዳ ሲደርሱ መሰረታዊ የጤና አግልግሎቶችን (ሆስፒታል መሄድንና ዶክተር ማየትን ጭምር) ማግኘት የሚያስችልዎት ጊዜያዊ የፌደራል የጤና ፕሮግራም አይኤፍኤች/IFH ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህም አገልግሎት የፀና የሚሆነው የክፍለሀገሩ ወይንም የቴሪተሪውን የጤና ፕሮግራም ለማግኘት ማሟላት የሚኖርብዎትን የጊዜ ገደብ እስኪያሟሉ ድረስ ነው። ይህም የሚፈጀው ጊዜ በአብዛኛው ሶስት ወር ያክል ሲሆን በዚህም ጊዜ ለሚኖሩበት ክፍለሀገር ወይንም ቴሪተሪ የጤና ዋስትና ፕሮግራም ተገልጋይ ለመሆን ማመልከት ይኖርብዎታል።

የህክምና አገልግሎት ሰጪዎችን ለማየት በሚሄዱበት ጊዜ ሁሉ የጊዜያዊ የፌደራል የጤና ፕሮግራም አገልግሎት ካርድዎትን ማሳየት ግድ ይላል። በየትኛውም የካናዳ አካባቢዎች ቢሆን የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ከተመዘገብ ማንኛውም የህክምና አገልግሎት ሰጪ የሚያስፈልግዎትን የህክምና አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። የተመዘገቡ አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር ኢንተርኔት ላይ “ጊዜያዊ የፌደራል የጤና ፕሮግራም አገልግሎት ሰጪዎችን ዝርዝር ፈልግ” በሚለው ስር ማግኘት ይቻላል።

የጊዜያዊ የፌደራል የጤና ፕሮግራም በሐኪም የታዘዘ መድሀኒትና በተጨማሪነት የተለያዩ አስቸኳይና መሰረታዊ አስፈላጊ የህክምና አገልግሎቶችን (ለምሳሌ የአይምሮ ጤና አግልግሎት፣ የአይን የማየት አቅም ውሱንነትና፣ አስቸኳይ የጥርስ ህመምና መበከልን/ኢንፌክሽን ማስታገስ) ይሸፍናል። የዚህን ተጨማሪ የህክምና አግልግሎትና በሐኪም የታዘዘ መድኃኒትን ወጪ የመሸፈን ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው የካናዳ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ፕሮግራም ወይንም የዚህ ተመጣጣኝ የሆነው የኪውቤክ ክፍለሀገር ፕሮግራም የገቢ ድጋፍ ተጠቃሚ ከሆኑ ብቻ ነው።

በጊዜያዊ የፌደራል የጤና ፕሮግራም የሚሰጡት አገልግሎቶችና ጥቅሞች አጠቃላይ ዝርዝር የካናዳ ኢሚግሬሽን ስደተኞችና ዜግነት መስርያቤት ዌብ ሳይት ላይ ማግኘት ይቻልላ።

አግልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የቤተሰብ ዶክተርና የጥርስ ሀኪም እንዲያገኙ በማድረግ በኩል ይረዱዎታል። በተጨማሪም አስፈላጊ ከሆነ የአእምሮ ጤናና መንፈስ ጭንቀት ችግር አማካሪዎችን አገልግሎቶችም እንዲያገኙ ያደርጋሉ።

ሁሉም ክፍለሀገራትና ቴሪተሪዎች የየራሳቸው የጤና ዋስትና (ኢንሹራንስ) አላቸው። የእርሶ ክፍለሀገር የጤና ኢንሹራንስ የምን ወጪዎችን እንደሚሸፍንልዎት ማወቅ ይኖርብዎታል። ካናዳ እንደገቡ አግልግሎት ሰጪዎቹ ለእርስዎ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ማግኘት እንዲችሉ ማመልከቻ ሙሙላትና ማስገባት ላይ ያግዙዎታል።
ለካናዳ አዲስ የሆኑ ስደተኞች ብዙ ጊዜ የብቸኝነትና ባይተዋርነት ስሜት ይሰማቸዋል። በርካታዎች ደግሞ ባሳለፉት መከራና ችግር ምክንያት ብሶትና ትካዜ (የስሜት ቁስል!) ያስቸግራቸዋል። ከእንደዚህ አይነት ህመም እንዲድኑ ያለክፍያ ሊያናግሯቸው የሚችሉ ሙያዊ ብቃቱ ያላቸው በርካታ አገልግሎት ሰጪዎች አሉ። በዚህ አንፃር እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ሊያገኙ ስለሚችሉት የአእምሮ ጤና የምክር ድጋፍ አይነት ይጠይቁ።

## ክትባት

ለተለያየ ህመም ክትባት መወጋት እራስን ለህመም ከመጋለጥ ለክፉ ጤና መዛባትና ያልጊዜ ቶሎ ከመሞት ለመጠበቅ በጣም አስተማማኝና ውጤታማ አርምጃ ነው።

ክትባት የሚሰራው ሰውነታችን የራሱ የሆነ ከህመም መከላከያ በመፍጠር ነው። ልክ እንደማንኛውም መድሀኒት ሁሉ የክትባት መድሀኒቶችም ለሕዝብ ከመቅረባቸው በፊት ጥብቅ የሆነ አጠቃላይ የብቃትና አስተማማኝነት ግምገማ ተደርጎባቸው ብቁ መሆናቸው ይረጋገጣል።

ወደ ካናዳ ከመምጣትዎት በፊት የወሰዷቸው ክትባቶትች የተሟሉ እንዲሆኑ ለካናዳ ኢሚግሬሽን የህክምና ምርመራ በአደርጉበት ወቅት ሐኪም ክትባቶች እንዲወስዱ ዕድል ይሰጡዎት ይሆናል። ይህን አገልግሎት መጠቀም በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው። ስለዚህም ካናዳ ከመግባትዎ በፊት ክትባት የሚያደርጉ ከሆነ የወሰዱትን ክትባት በሙሉ የሚያሳይ ሰነድ ይዘው ካናዳ መምጣት እንዳለብዎት አይዘንጉ።

አንድ ጊዜ ካናዳ ከገቡ በኋላ የሚኖሩበት ክፍለሀገር ወይንም ቴሪተሪ የጤና ኢንሹራንስ ለበርካታ የክትባት አይነቶች ይከፍላል። በተለይ ከአሁን ቀደም እርስዎና ቤተሰብዎ ክትባቶች ወስዳችሁ ካልሆነ በክትባት ሊከላከሉት ለሚችሉት ለበርካታ ህመም ልትጋለጡ ትችላላችሁ። በተለይ ፃ

ሕፃናትና ትንንሽ ልጆች ሊከላከሉት ለሚችሉት ለበርካታ ህመም ሊጋለጡ ይችላሉ። በአንዳንድ የካናዳ አካባቢዎች ሕጻናት አስፈላጊውን ክትባት በሙሉ አጠናቀው ያልወሰዱ ከሆነ ትምህርትቤትና መዋዕለ ሕፃናት መግባት አይፈቀድላቸውም።

አገልግሎት ሰጪዎች፣ ዶክተሮችና፣ ሌችም የህክምና ባለሙያዎች ቤተሰብዎ የተሟላ ክትባት እንዲኖራችሁ ለማገዝ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡዎት ይችላሉ።

የእራስዎትንና የቤተሰብዎን ክትባት የተሟላ የማድረግ ውሳኔና ሀላፊነት የእርስዎ ነው። እርስዎ ክትባት ለመከተብ ሲወስኑ እራስዎትን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በተለይም በቀላሉ ለህመም ሊጋለጡ የሚችሉ ሰዎችን ጭምር ከመታመም እየተከላከሉ እንደሆነ አለመዘንጋት ያስፈልጋል፡፡

## ምግብና ውሃ



ካናዳ ውስጥ ውሀ ያለስጋት መጠጣት ይችላሉ። እያንዳንዱ ቤት የራሱ የሆነ በቧምቧ የሚመጣ ሙቅና ቀዝቃዛ ውሃ አለው። ቀንም ይሁን ለሊት ውሃ ማግኘት ይችላሉ።

በየአካባቢው ገበያ ላይ የሚገኘው የምግብ አይነት ብዛት የሚወሰነው በሚኖሩበት አካባቢ ነው። የተለያየ ሕብረተሰብ ያለባቸው ትልልቅ ከተሞች አብዛኛውን እርስዎ ብዙ ጊዜ የሚመገቡትን የምግብ አይነት ሊያገኙ ይችላሉ። በአንጻሩ ትንንሾቹ ከተሞች የሚኖራቸው ምርጫ ውሱን ይሆናል።

ካናዳ ከተለያየ ጎሳና ባሕል የመጡ ሰዎች ይኖራሉ። በዚህም ምክንያት ከተለያየ ባህል የሚመጡ በርካታ የምግብ አይነቶች ማግኘት ይቻልላ። በተለመደው ትልልቅ የሸቀጥ ሱቆች የማይገኙ የምግብ አይነቶችን የሚሸጡ ሱቆችም ስላሉ የሚፈልጉትን የምግብ አይነት ሊያገኙ ይችላሉ። አንዳንዶቹ የምግብ ሸቀጦች ዋጋቸው እርሶ ከለመዱት በላይ ውድ ሁነዉ ሊያገኙ ይችላሉ። ለዚህም ምክንያቱ የካናዳ የአየር ፀባይና ብዙ የምግብ አይነቶች ከሌሎች ሀገሮች መምጣት ስላለባቸው ነው።

## ሃይማኖት





ካናዳ ብዙ የተለያዩ ሃይማኖቶች አሉ። አርስዎም የእራስዎትን ሃይማኖት በነጻነት መከተል የሚችሉ ሲሆን የሌሎችን ሃይማኖት ማክበር እንዳለብዎት ደግሞ የካናዳ ሕግ ያስገድዳል። ሃይማኖትዎን እንዲቀይሩ ማንም አይጠየቅዎትም ሊያስገድድዎትም አይችልም። የሃይማኖት ነጻነት ከካናዳ መሰረታዊ መብቶች አንዱ ነው።

ብዙ የግል ስፖንሰር አድራጊዎች ከሀይማኖታዊ ስብስቦች ጋር ቁርኝት ቢኖራቸውም እርስዎ የግል ሀይማኖትዎን በነፃነት መከተል ይችላሉ። እነኚህ ነፃ አገልግሎት ሰጪ ሰዎች ብቸኛ ፍላጎታቸው እርስዎ ካናዳ መጥተው የተመቻቸ ኑሮ በተሳካ መንገድ እንዲመሰርቱ ማድረግ ነው። ይህን እገዛ ስላደርጉልዎት ከእርስዎ በግዴታነት የሚጠብቁት ምንም ነገር የለም።

## የአየር ፀባይ









ካናዳ አራት የዓመት ወቅቶች አሏት። እነዚህም ፀደይ፣ በጋ፣ በልግና ክረምት ናቸው። ካናዳ በጣም ሰፊ ሀገር በመሆኗ በየወቅቱ ያለው የአየር ፀባይ ከክፍለ ሀገር ክፍለሀገር የተለያየ ሊሆን ይችላል። ፀደይ (መጋቢት፣ ሚያዝያና፣ ግንቦት) በአብዛኛው የካናዳ ክፍል ዝናባማና ቀዝቀዝ ያለ ይሆናል።

በበጋ (ሰኔ፣ ሐምሌና፣ ነሐሴ) የአየር ጠባዩ በአብዛኛው የሀገሪቷ ክፍሎች በጣም ሞቃታማ ይሆናል። ቀን ቀን ላይ ብዙውን ጊዜ ሙቀቱ ከ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ ሲሆን አንዳንዴ ከ30 ዲግሪ ሴንቲግሬድም ሊበልጥ ይችላል።
በልግ (መስከረም፣ ጥቅምትና፣ ህዳር) ላይ የአየሩ ፀባይ በጣም ዝናባማና ቀዝቀዝ ያለ ሊሆን ይችላል። በክረምት ወራት (ታሕሳስ፣ ጥርና የካቲት) ደግሞ በአብዛኛው ስፍራ ብዙን ጊዜ በጣም ቀዝቃዛ ሲሆን ቅዝቃዜው ከዜሮ ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች ይሆናል። ከታህሳስ አካባቢ ጀምሮ እስከ 10

መጋቢትና ሚያዚያ ድረስ በረዶ መሬቱን ይሸፍነዋል። በደቡብ ምዕራብ ብሪትሽ ኮሎምቢያ ክፍለሀገር (ቪክቶሪያና ቫንኩቨር አካባቢ) በክረምት ከበረዶ ይልቅ ዝናብ ይበዛል።

እንደመጡበት ሀገር የአየር ፀባይ ሁኔታ በመጀመሪያው የካናዳ ክረምት ቅዝቃዜና በርዶ በጣም ሊደነቁና ግራ ሊጋቡ ይችላሉ። ቅዝቃዜውን የሚመጥን ልብስ በአግባቡ የሚለብሱ ከሆነ የካናዳን ልዩ የክረምት ውበት ሊደሰቱበት ይችላሉ። ካናዳ ሲመጡ (በተለይም በክረምት አካባቢ ከመጡ) ለካናዳ ብርድ የሚሆን ልብስ ሊሰጥዎ ይችላል። አገልግሎት ሰጪዎቹም ለቤተሰብዎ ኮፍያ፣ የክረምት ረጅም ጫማ፣ ጓንትና የክረምት ካፖርት፣ መግዛት ላይ እገዛ ያደርጉልዎታል።

# የመጨረሻ የምክር ቃላት

አዲስ ሕይወት በካናዳ መጀመር አስደሳችና ብዙ አዳዲስ ዕድሎችንም የሚያስገኝ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ አዳጋች ሁኔታዎችም ይኖራሉ። ለአንዳንድ ሰዎች መላመዱ በጣም አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። አዲስ ሀገር መላመድ ጊዜ ስለሚፈልግ ታጋሽ ለመሆን ይሞክሩ። ልክ እንደ እርስዎ አዲስ ሁነው የመጡ ሰዎች ሀገሩን ተላምደው ከተቀረው የካናዳ ኅብረተሰብ ጋር ሙሉ ለሙሉ በመዋሀድ መኖር መቻላቸውን ሁሌ ያስታውሱ።

የሚያስፈልግዎትን እገዛ የሚያደርጕልዎት ሰዎችና አገልግሎቶች ወይንም ፕሮግራሞች አሉ። የሚኖርዎትን ማንኛቸውንም ጥያቄዎችና ስጋት ወይንም ሀሳብ አድምጠው ምላሽ የሚሰጡ ሰዎችና አገልግሎቶች አሉ። የእነኝህ አገልግሎት ሰጪዎች ፍላጎትም ለእርስዎ የሚበጅ ነገር ማድረግ ነው። ማመልከቻዎትን በተመለከተ ጥያቄ ካለዎት ደግሞ ጥያቄዎቹን ለካናዳ የእምግሬሽን የስደተኞችና የዜግነት ቢሮ ማቅረብ ይችላሉ።

ለተጨማሪ አገልግሎት ደግሞ የማህበረሰብ ስብስቦች፣ የሀይማኖት ስብስቦችና፣ የምክር አገልግሎት ሰጪዎች አሉ። እነሱም ካናዳ በነዋሪነት የሚመጡ አዳዲስ ሰዎች ከማህበረሰቡ ጋር በደንብ ተዋህደው መኖር እንዲችሉ የማገዝ ከፍተኛ ልምድ አላቸው። እርዳታ በሚያስፈልግዎት ጊዜ ሁሉ እርዳታ ከመጠየቅ ወደኋላ አይበሉ።

በማንኛውም ወቅት ከአግባብ ውጭ በሆነ መንገድ በደል ወይንም ብዝበዛ ደርሶብኛል ብለው ካመኑ ለካናዳ የፍልሰት የስደተኞችና የዜግነት ቢሮ በአስቸኳይ በዚህ አድራሻ ያሳውቁ IRCC.INSPR-PPPRRI.IRC@CIC.GC.CA

ከካናዳ የኢምግሬሽን የስደተኞችና የዜግነት ቢሮ ጋር ግንኙነት በማድረግዎ ምክንያት የካናዳ ነዋሪነት መብትዎን የሚያጡበት ምንም አጋጣሚ ወይንም ምክንያት የለም።

በመጨረሻም እርስዎ ለሚያደርጕት ዝግጅት ሊያግዙዎት የሚችሉ ጠቃሚ መረጃ ያላቸው በርካታ የኢንተርኔት ገፆች ወይንም ዌብ ሳይቶች አሉ። የየክፍለሀገራቱ የኢንተርኔት ገፆች ወይንም ዌብ ሳይቶች ብዙ ጊዜ የሚነሱ ጥያቄዎችን የተለያዩ የማህበረሰብ ስብስቦች ኢንተርኔት ገፅ መስፈንጠሪያዎች (ሊንኮች) ዜናዎችና አንዳንድ ዝግጅቶችን የመሳሰሉ መረጃዎች ይይዛሉ።

የካናዳ መንግስት የኢንተርኔት ገፆች ወይንም ዌብ ሳይቶች የሚከተሉትን ጨምሮ በበርካታ ርዕሶች ላይ መርጃ አላቸው። ሕይወት በካናዳ ምን እንደሚመስል፣ በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል አዲስ የሚሰፍሩ ሰዎችን ለማቋቋም የሚሰሩ ድርጅቶች ዝርዝርና ካርታ፣ በነፃ የሚደረግ የቋንቋ ብቃት ፈተናንና፣ የቋንቋ ትምህርት አገልግሎት; ወደ ካናዳ ለመምጣት ለሚያደርጕት ዝግጅት የሚረዳ መረጃ ።

www.canada.ca/immigration